# ፒስ አነስተኛ የገንዘብ ተቋም አክሲዮን ማህበር
## የባለአክሲዮኖች 5ኛ ድንገተኛ ጉባኤ
## ቃለ ጉባኤ ቁጥር 5

1. ጠቅላላ ጉባኤው የተደረገበት ቦታ፣ ቀንና ሰዓት

ቦታ:- ግሎባል ሆቴል (አዲስ አበባ)
ቀን:- ታህሳስ 1/2009 ዓ.ም.
ሠዓት:- ከቀኑ 5:30 - 6:30 ሰዓት

2. የጉባኤው ጥሪ አደራረግ፣

ይህ የባለአክሲዮኖች 5ኛ ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባዔ የተጠራው በንግድ ህግ አንቀጽ 392 መሠረት ሆኖ ከጉባዔው ዕለት 15 ቀናት አስቀድሞ በደብዳቤ ቁጥር PEACE200/16 በNovember 11/2016 በተፃፈ እና በአድራሻ በተላከ ደብዳቤ በተጨማሪም በስልክ ተጠርተዋል፡፡

3. የጉባኤው ጽ/ቤት አባላት እና በጉባኤው የተገኙ አስተዳዳሪዎች

3.1 የጉባኤው ጽ/ቤት አባላት፣

| ተ/ቁ | ስም | ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌታቸው ወርቁ ወ/ማርያም | የጉባኤው ሰብሳቢ |
| 2 | አቶ መስፍን ተፈራ | ድምፅ ቆጣሪ |
| 3 | ወ/ሮ አለምነሽ ኃ/ማርያም | ድምፅ ቆጣሪ |
| 4 | አቶ ተዘራ ከበደ በቀለ | ፀሐፊ |

3.2 በጉባኤው የተገኙ አስተዳዳሪዎች፣

| ተ/ቁ | የአስተዳዳሪዎች ስም | በአስተዳደር ምክር ቤት (ቦርድ) ውስጥ ያለው ኃላፊነት | የአስተዳዳሪው ወይም የተወካይ አስተዳዳሪ ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌታቸው ወርቁ ወ/ማርያም | የቦርድ ሊቀመንበር | |
| 2 | አቶ ማሞ ከበደ ሸንቁጥ | የቦርድ አባል | |
| 3 | ዶ/ር አሰፋ ወ/ጊዮርጊስ ይልማ | የቦርድ አባል | |
| 4 | ወ/ሮ ፍሬህይወት ገበየሁ ሰሚነው | የቦርድ አባል | |
| 5 | አቶ ኤፍሬም አላምረው | የቦርድ አባል | |

NATIONAL BANK OF ETHIOPIA
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
53

The FDRE M... Authentication and Registration Office
የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፍትህ ሚኒስቴር የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት

### 3.3 በጉባኤው ያልተገኙ አስተዳዳሪዎች፣

| ተ/ቁ | ስም | ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1 | ሲ/ር መሠረት ሽፈራው ይብራሁ | አባል |
| 2 | ወ/ሮ ፍላጐት ለማ ክብረት | አባል |

### 3.4 በጉባኤው የተገኙ ታዛቢዎች

| ተ/ቁ | ስም | የወከሉት ድርጅት |
|---|---|---|
| 1 | ወ/ሮ ሸዋዬ ገ/መድን | ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሰነዶች ምዝገባ እና ማረጋገጫ ጽ/ቤት |
| 2 | ወ/ሮ እመቤት ይመር | ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሰነዶች ምዝገባ እና ማረጋገጫ ጽ/ቤት |
| 3 | አቶ በለጠ ዘገየ | ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ |

4. ምልዓተ ጉባኤ፣
   - 4.1. ጠቅላላ የማኅበሩ አባላት ብዛት 16
   - 4.2. ጠቅላላ የማኅበሩ የተፈረመ አክስዮን ብዛት 25000
   - 4.3. በስብሰባው የተገኙ አባላት ብዛት10የያዙት አክስዮን ብዛት19724(78.9%)
   - 4.4. በስብሰባው ያልተገኙ አባላት ብዛት6የያዙት አክስዮን ብዛት 5276( 21.1 %)
   - 4.5. ለጉባኤው አስፈላጊ የሆነ የአክስዮን ብዛት 12500 (50%)

በዚሁ መሰረት በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 22 እና በንግድ ህጉ አንቀጽ 425 መሠረት ከማህበሩ ባለአክስዮኖች 78.9% የተገኙ ስለሆነ በጉባዔው አጀንዳ ላይ ተወያይተው ውሣኔ ማሳለፍ ሥልጣን ያላቸው መሆኑ ተረጋግጦ ጉባዔው ቀጥሏል፡፡ በጉባኤው ላይ የተገኙትንና ያልተገኙትን ባለአክሲዮኖች ስም ዝርዝርና የያዙትን አክስዮን መጠን የያዘ ሠንጠረዥ (Attendance Sheet) (ሠንጠረዥ-1) ከዚህ ቃለ-ጉባኤ ሰነድ ጋር ተያይዟል፡፡

በንግድ ህግ አንቀጽ 405 መሠረት በጉባኤው ላይ ለድምጽ ቆጣሪነት ከባላአክሲዮኖች ውስጥ ብልጫ አክሲዮን ያላቸው ሁለት አባላት ድምጽ ቆጣሪ ሆነው እንዲመረጡ ተጠይቆ፤ የአክሲዮን ብልጫ ያላቸው ከማህበሩ አባላት ውስጥ ሁለት አባላት ብቻ ሲሆኑ እነዚህ አባላት የድምጽ ቆጣሪነት መብታቸውን ለመጠቀም አለመፈለጋቸውን የገለጹ ሲሆን የቦርድ ሰብሳቢ እና የቦርድ አባል በመሆናችን ጠቅላላ ጉባኤው ከእኛ ውጭ ሌላ የድምጽ ቆጣሪ እንዲመርጥ ሲሉ ሀሳብ በመስጠታቸው ሁለት ድምጽ ቆጣሪ በምርጫ ተመርጠዋል፡፡

5.የጉባዔው አጀንዳዎች

5.1. የጉባኤውን አጀንዳ ማጽደቅ፤
5.2. የጠቅላላ ጉባኤ የሚደረግበትን ጊዜ በንግድ ህጉ አንቀጽ 418 መሠረት እስከ ስድስት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ማድረግ እንዲቻል በመተዳደሪያ ደንብ ውስጥ ይህንን የተመለከተ ደንብ ማካተት፡፡
5.3. በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ የተጠቀሰው የተቋሙ የበጀት ዓመት ማስተካከል
5.4. የጉባኤውን ቃለ ጉባኤ ማጽደቅ ናቸው፡፡

6. የጉባኤው ውይይት አጭር ቃልና ውሣኔ፣

6.1 አጀንዳ 5.1 የጉባኤውን አጀንዳ ማጽደቅ

6.1.1 የውይይቱ አጭር ቃል

የጉባኤው ሰብሳቢ ጉባኤው ሊነጋገርባቸው ይገባል በማለት የቀረቡትን አጀንዳዎች በዝርዝር በማስረዳት ሊጨመር ወይም ከአጀንዳሊወጣ የሚገባ ካለ በማለት ጉባኤውን በመጠየቅ ፤ከጉባኤው የሚጨመር አጀንዳ ባለመኖሩ ለውሳኔ አቅርበዋል፡፡

6.1.2 ውሣኔ፣

ጉባኤው የቀረቡትን አጀንዳዎች በሙሉ ድምጽ አፅድቋል፡፡

6.2 አጀንዳ 5.2. የጠቅላላ ጉባኤ የሚደረግበትን ጊዜ በንግድ ህጉ አንቀጽ 418 መሠረት እስከ ስድስት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ማድረግ እንዲቻል በመተዳደሪያ ደንብ ውስጥ ይህንን የተመለከተ ደንብ ማካተት፡፡

6.2.1 የውይይቱ አጭር ቃል

የጠቅላላ ጉባኤ የሚደረግበትን ጊዜ የበጀት ዓመቱ ከተናቀቀ ሐምሌ አንድ ጀምሮ እስከ ስድስት ወር ባለ ጊዜ ውስጥ ማድረግ እንዲቻል በመተዳደሪያ ደንብ ውስጥ ይህንን የተመለከተ ደንብ ማካተት በንግድ ህጉ አንቀጽ 418 ንኡስ ቁጥር 2 መሠረት የሚቻል በመሆኑ ደንቡ ውስጥ ይህንን ማካተት የሚጠቅም መሆኑ ታምኖበታል፡፡

በተለይ የተቋሙ ባለአክሲዮኖች ውስን በመሆናቸው አስቀድሞ ለማሳሰብ ፤እንዲሁም የውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት በሚዘገይበት ወቅት ፤ የሥራ ጫና በሚበዛበት ወቅት የጠቅላላ መደበኛ ጉባኤ ለማድረግ በቂ ጊዜ መኖሩ ጠቃሚ ስለሚሆን በህጉ የተቀመጠውን እስከ ስድስት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ማድረግ እንዲቻል መውሰዱ ታምኖበት
በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የተቋሙ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ መደበኛ ጉባኤ የሂሳብ ዓመቱ ከተጠናቀቀ ከሐምሌ 1 ጀምሮ እስከ ስድት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ይደረጋል ፡፡ በሚል እንዲገባ ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ ስምምነቱን ለውሳኔ አሳልፏል፡፡

6.2.2 ውሣኔ

የተቋሙ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ መደበኛ ጉባኤ የሂሳብ ዓመቱ ከተጠናቀቀ ከሐምሌ 1 ጀምሮ እስከ ስድት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ይደረጋል ፡፡ የሚል ተጨማሪ ደንብ በተቋሙ መተዳደሪያ ደንብ እንዲገባ ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

6.3 አጀንዳ 5.3 በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ የተጠቀሰው የተቋሙን የሒሳብ ዓመት ከጥር 1 እስከ ታህሳስ 30 የሚለውን ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 በሚል ማስተካከል፡፡

6.3.1 የውይይቱ አጭር ቃል

በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ የተጠቀሰው የበጀት ዓመት በመንግስት አዋጅ የተቀየረ ሲሆን ተቋሙም በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ የተጠቀሰው ቢኖርም በሥራ ላይ ያለውና ተቋሙ በአሁኑ ጊዜ የሚከተለው በመንግስት አዋጅ የተጠቀሰውን ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 መሆኑ የታወቀ ቢሆንም በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ የተገለጸው የተቀየረ መሆኑን መጥቀስ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት ለውሳኔ ቀርቧል፡፡

6.3.2 ውሳኔ

የተቋሙ የበጀት በዓመት ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 መሆኑ ተጠቅሶ በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 18 ላይ ከጥር 1 እስከ ታህሳስ 30 በሚል የተገለጸው የተሻረ እና ለረዥም ጊዜ በሥራ ላይ ያለነበረ በመሆኑ ከመተዳደሪያ ደንቡ እንዲወጣ ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

7. ለጉባኤው የቀረቡ ሰነዶች፣

7.1 የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA
53

8. የጉባኤ ጽ/ቤት አባላት ማረጋገጫ

እኛ <u>የፒስ አነስተኛ የገንዘብ ተቋም</u> አክሲዮን ማህበር የጉባኤ ጽ/ቤት አባላት ከዚህ ቃለ-ጉባኤ ሠነድ ጋር አባሪ ሆኖ በተያያዘው የመጥሪያ ሠነድ (Attendance Sheet) ላይ ስማቸው፣ የፈረሟቸው እና የከፈሏቸው አክሲዮኖች ብዛት በየስማቸው አንፃር በተመለከቱት ትይዩ ራሳቸው ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው የፈረሙ ባለአክሲዮኖች በታህሳስ 1 ቀን 2009 ዓ.ም. በተካሄደው የአክሲዮን ማህበሩ <u>5ኛ</u> ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ መገኘታቸውንና በዚህ ቃለ-ጉባኤ ሠነድ ላይ የተገለፁትን ውሣኔዎች ማሣለፋቸውን በሙሉ ስምና ፊርማችን አረጋግጠናል፡፡

| ተ/ቁ | የጉባኤ ጽ/ቤት አባላት ስም | ኃላፊነት | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌታቸው ወርቁ ወ/ማርያም | የጉባኤው ሰብሳቢ | |
| 2 | አቶ መስፍን ተፈራ | ድምፅ ቆጣሪ | |
| 3 | ወ/ሮ አለምነሽ ኃ/ማርያም | ድምፅ ቆጣሪ | |
| 4 | አቶ ተዘራ ከበደ በቀለ | ፀሐፊ | |

## 9. የአስተዳዳሪዎች ማረጋገጫ

እኛ የፒስ አነስተኛ የገንዘብ ተቋም አክሲዮን ማህበር አስተዳዳሪዎች ከዚህ ቃለ-ጉባኤ ሠነድ ጋር አባሪ ሆኖ በተያያዘው የመጥሪያ ሠነድ (Attendance Sheet) ላይ ስማቸው፣የፈረሟቸው እና የከፈሏቸው አክሲዮኖች ብዛት በስማቸው አንፃር በተመለከቱት ትይዩ የፈረሙ ባለአክሲዮኖች በታህሳስ 1 ቀን 2009 ዓ.ም. በተካሄደው የአክሲዮን ማህበሩ 5ኛ ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ መገኘታቸውንና ራሳቸው ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በዚህ ቃለ-ጉባኤ ሠነድ ላይ የተገለፁትን ውሣኔዎች ማሣለፋቸውን በሙሉ ስምና ፊርማችን እያረጋገጥን፣ በሰነዶቹ ላይ ስለተገለፁት ጉዳዮች እና ስለተላለፉት ውሣኔዎች ትክክለኛነት ስማቸው በሰነዶቹ ላይ በተዘረዘሩት ሰዎችም ሆነ በሌላ በጉዳዩ ያገባኛል በሚል ወገን ለሚነሳ ማናቸውም የመብት ጥያቄ ኃላፊዎች መሆናችንን ጭምር እናረጋግጣለን፡፡

| ተ/ቁ | የአስተዳዳሪዎች ስም | በአስተዳደር ምክር ቤት (ቦርድ) ውስጥ ያለው ኃላፊነት | የአስተዳዳሪው ወይም የተወካይ አስተዳዳሪ ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌታቸው ወርቁ ወ/ማርያም | የቦርድ ሊቀመንበር | |
| 2 | አቶ ማሞ ከበደ ሸንቁጥ | የቦርድ አባል | |
| 3 | ዶ/ር አሰፋ ወ/ጊዮርጊስ ይልማ | የቦርድ አባል | |
| 4 | ወ/ሮ ፍሬህይወት ገበየሁ ሰሚነው | የቦርድ አባል | |
| 5 | አቶ ኤፍሬም አላምረው | የቦርድ አባል | |

# ሰንጠረዥ 1

## ፒስ አነስተኛ የገንዘብ ተቋም አ.ማ
## የባለአክሲዮኖች 5ኛ ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ
## በጉባኤው ላይ የመገኘት ማስረጃ ወረቀት

| ተ.ቁ. | ስም ከነአያት | አድራሻ | የአክሲዮኖች ብዛት | | | የባለአክሲዮኑ ወይም የወኪሉ ስምና ፊርማ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የተፈረመ | የተከፈለ | ያልተከፈለ የለም | |
| 1 | አቶ ጌታቸው ወርቁ ወ/ማርያም | ቦሌ ክ/ከ ቀ. 02 አ.አ የቤት ቁ. 893 | 2,453.00 | 2,453.00 | | |
| 2 | አቶ ማሞ ከበደ ሸንቁጥ | አራዳ ክ/ከ ቀ. 19 አ.አ. የቤ.ቁ. 703 | 2,453.00 | 2,453.00 | | |
| 3 | ዶ/ር አሰፋ ወ/ጊዮርጊስ ይልማ | ቦሌ ክ/ከ አ.አ. የቤ.ቁ. 2111 | 2,452.00 | 2,452.00 | | |
| 4 | አቶ መስፍን ተፈራ ወ/ገብርኤል | የካ ክ/ከ ቀ. 03 አ.አ. የቤ.ቁ. 1843 | 2,452.00 | 2,452.00 | | |
| 5 | ወ/ሮ ፀሀይ ፀጋዬ መከተ | የካ ክ/ከ ቀ. 13/14 አ.አ. የቤ.ቁ. 092 | 2,452.00 | 2,452.00 | | ያልተገኘ |
| 6 | ወ/ሮ ለበሰች ጸጋ ባለህ | የካ ክ/ከ ቀ. 13/14 አ.አ. የቤ.ቁ. 100 | 2,452.00 | 2,452.00 | | ያልተገኘ |
| 7 | ወ/ሮ ጽጌ ሃይሌ ወ/ጊዮርጊስ | ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ ቀ. 12/13 አ.አ. የቤ.ቁ. 415 | 2,452.00 | 2,452.00 | | |
| 8 | ወ/ሮ አለምነሽ ኃ/ማርያም ባዲሾ | የካ ክ/ከ ቀ. 08/15 አ.አ. የቤ.ቁ. 350 | 2,452.00 | 2,452.00 | | |
| 9 | አቶ ኤፍሬም አላምረው ቦጋለ | ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከ ቀ. 15/16 አ.አ. የቤ.ቁ. 38/137 | 2,452.00 | 2,452.00 | | |
| 10 | አቶ ተዘራ ከበደ በቀለ | ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ ቀ. 15 አ.አ የቤ.ቁ. 1287 | 2,452.00 | 2,452.00 | | |
| 11 | አግሪ ሰርቪስ ኢትዮጵያ | ቂርቆስ ክ/ከ ቀ. 03 አ.አ. የቤ.ቁ. 379 | 129 | 129 | | ያልተገኘ |
| 12 | ወ/ሮ ፍሬህይወት ገበየሁ ሰሚነው | ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ.ከ ቀ 04 አ.አ. የቤ.ቁ. 1191 | 81 | 81 | | |
| 13 | ሲ/ር መሠረት ሺፈራው ይብራሁ | ቦሌ ክ/ከ ቀ. 19/19/20 አ.አ. የቤ.ቁ. 616 | 81 | 81 | | ያልተገኘ |
| 14 | ወ/ሮ ሰላማዊት አበበ ተጫኔ | አራዳ ክ/ከ 2 ቀ. 10 አ.አ. የቤ.ቁ. 184 | 81 | 81 | | ያልተገኘ |
| 15 | ወ/ት ፍላጐት ለማ ክብረት | አዲስ ከተማ ክ/ከ ቀ. 19/20 አ.አ. የቤ.ቁ. 099 | 81 | 81 | | ያልተገኘ |
| 16 | አቶ አክሊሉ ታደሰ አሻሚ | ወ. 2 ቀ. 05 ሻሸመኔ የቤ.ቁ. 411 | 25 | 25 | | |

የአስፈራሚው ስም ____________ የአስፈራሚው ስም ____________

ፊርማ ____________ ፊርማ ____________

NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

The FDRE Authentication and Registration Office

በኢፌዲሪ የፍትህ ሚኒስቴር
የሰነዶች ማረጋገጫ ጽ/ቤት
አዲስ አበባ (ዋናው መሥሪያ ቤት)
ቁጥር ሰ/መ/1806/4ሐ/2010
በጽሕፈት ቤቱ ቀርበው ፈርመዋል።
አዲስ አበባ 3/13/ ቀን 2009 ዓ.ም.

ሸዋዬ ገ/መድህን ደስታ
SHEWAYE G/MEDHIN DESTA
የሰነዶች ማረጋገጫ ኦፊሰር
Documents Authentication Officer
13/09

* በኢፌዴሪ የፍትህ ሚኒስቴር የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት *
The FDRE Ministry of Justice Documents Authentication & Registration Office

በኢፌዲሪ የፍትህ ሚኒስቴር
የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት
አዲስ አበባ

የቴምብር ቀረጥ ማረጋገጫ ማህተም
የተከፈለበት ምክንያት ______
የገንዘቡ ልክ ብር 165
በፊደል ______
ወይም ብር ___ የሆነ ቴምብር ተለጥፏል።
የደረሰኝ ቁጥር 617672
3/13 ቀን 20 09 ዓ.ም
የቴምብር ቀረጥ መብት አስፈጻሚ
ስም ______
ፊርማ ______